# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 343 ህዳር 26 2007 ገጽ


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ህወሃቶች እኛ ከሌለን ይህችን አገር እንበትናታለን፤ ይህችን አገር የምንሰብር እኛ የምንጠግን እኛ እያሉ እንደሚያሚርቱ ሰምተናል። እኛ የቀረፅነው ፖሊስ ከሚቀየር ሞታችንን እንመርጣለን እያሉ ማቅራራታቸውም ከህዝብ የተሰወረ ነገር አይደለም። የህወሃት ፖሊሲ የሚቀየረው በመቃብርችን ላይ ነው የሚል የማይናወፅ አቋማቸው መቼም ቢሆን በሠለጠነ መንገድ በውይይትና በድርድር እንደማይቀየር ደጋግመው አሳይተውናል።

ግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ወያኔ ከመጭው የይስሙላ ምርጫ ድራማ ጋር በተያያዘ ውጥረት ውስጥ መግባቱ ታወቀ

እብሪተኛው ወያኔ ለመጭው የይስሙላ ምርጫ ተብየ ድራማው ማስፈጸሚያ በሚል በድጋፍ መልክ ከአውሮፓ ህብረት ያጋብስ የነበረው ከፍተኛ ገንዘብ መታገቱን ተከትሎ አገዛዙ ውጥረት ውስጥ መግባቱን የውስጥ ምንጫችን ያደረሰን መረጃ ያመለክታል። ፋሽስቱ ወያኔ በንጹሃን ዜጎች ላይ እያደረሰ የሚገኘው አስከፊ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እየተባባሱ መምጣታቸውን ተከትሎ የተለያዩ አለማቀፍ መንግስታት፤ የሰብአዊ መብት ድርጅቶችና የህግ አካላት በተከታታይ የውግዘት መግለጫ ማውጣታቸው የሚታወቅ ሲሆን የአውሮፓ ህብረት በተቋማቱ የወጡ መግለጫዎችን እንዲሁም በፋሺታዊ አገዛዝ ላይ በአገር ቤት እና በውጭ አገራት በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እየተሰነዘሩ የሚገኙት የተቃውሞ ትዕይንቶች በግንቦት ወር ለሚካሄደው ምርጫ ማስፈጸሚያነት ሊሰጥ የነበረውን ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ እንዲያዘገይና እንዲያጤን ማስገደዳቸውን ለማወቅ ተችሏል። በእብሪተኛው ወያኔ ላይ ከተለያዩ አካላት በመቅረብ ላይ ያሉ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በህብረቱ ምርመራ እየተካሄደባቸው እንደሚገኝም ያገኘነው መረጃ ያሳያል።

በአዲስ አበባ ብቻ ከ 200 በላይ ንጹሃን ኢትዮጵያውያን በጠራራ ጸሃይ በጥይት ተደብድበው ለተገደሉበት የ 1997 ቱ ምርጫ የአውሮፓ ህብረት ከ3 ሚሊዮን ዩሮ በላይ ድጋፍ አድርጎ እንደነበር የሚታወስ ሲሆን ህብረቱ ለዘንድሮው የወያኔ የግንቦት ወር የይስሙላ የምርጫ ድራማ ተመሳሳይ ድጋፍን ለማድረግ እቅድ ይዞ እንደነበር ምንጮቻችን አመልክተዋል። የአውሮፓ ህብረት ለጉጅሌው ወያኔ የሚሰጠውን የገንዘብ ድጋፍ በማዘግየቱ ምክንያትም የወያኔው የምርጫ ቦርድ ተብየ ካዝና ባዶ በመሆኑና ለምርጫው ማካሄጃ በጀት ባለመኖሩ ቅጥረኛ ሹማምንቱ ተፋጠው እንደሚገኙ ለማወቅ ችለናል።

## ደቡብ ክክክ በዳውሮ አካባቢ ተዳፍኖ የቆየዉ ግጭት እንደገና አገረሸበት

በደቡብ ክልል ዳውሮ ዞን ከአመታት አመት በፊት ተቀስቅሶ የነበረው የመልካም አስተዳደር እጦት ጥያቄ እልባት ባለማግኘቱ ጥያቄው በዩሰአዲስ መልክ ማገርሸቱንና መቀረብ መጀመሩን ተከትሎ በዞኑ ውጥረት መንገሱን ከአካባቢው የተላከልን መረጃ ያመልክታል። እንደ ምንጫችን ዘገባ የዞኑ ነዋሪዎች ከፍተኛ የሆነ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዳሉባቸው በመግለጽ ላይ መሆናቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በአዲስ መልክ መነሳት የጀመረውን የህዝብ ጥያቄ ተከትሎም አገዛዙ ቅጥረኛ የፌደራል ፖሊስ አባላትንና አድማ በታኝ ሃይሎችን በአካባቢው ማስፈር መጀመሩን ለማወቅ ተችሏል።

በዳውሮ ዞን የተቀሰቀሰውን የመልካም አስተዳደር እጦት ተከትሎ ውጥረቱ ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ በመምጣቱ ቅጥረኛ የፌደራል ፖሊሶች በነዋሪዎች ላይ የከፋ እርምጃ መውሰድ ሊጀምሩ ይችላሉ በሚል ስጋት የወደቁ በርካታ ሰዎች ወደ አጎራባች ዞኖችና ቀበሌዎች መሰደድ መጀመራቸው ታውቋል። ከዚህ በተጨማሪ በዞኑ የሚገኙ አብዛኞቹ ትምህርት ቤቶች የተዘጉ ሲሆን ህዝቡ ከዞኑ የወያኔ ቅጥረኛ ሹማምንት ተወካዮች ጋር ጥያቄያቸው መፍትሔ ካላገኘ ለመነጋገር እንደማይፈልጉ በመግለጽ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል። አዲስ በተቀሰቀሰው የህዝብ ቁጣና ብሶት አንዳንድ የዞኑ ቅጥረኛ ካድሬዎች ሳይቀር ከህዝቡ ጎን በመሰለፍ በስውር ድጋፍ እየሰጡ መሆናቸውንም ዘጋቢያችን ገልጿል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ከሁለት ዓመት በፊት የዋካን ከተማ ወደ ዞንነት እንድትቀየር በተነሳ ጥያቄ በዞኑ በርካታ ሰዎች በግፍ መረሸናቸው የሚታወስ ሲሆን በዞኑ ከእለት እለት እየተንሰራፋ የመጣውን የመልካም አስተዳደር እጦት በመቃወም የአካባቢው ነዋሪ የነበረው መምህር የኔሰው ገብሬ እራሱን በእሳት አቃጥሎ መሰዋቱ ይታወሳል፡፡

## አሶሳ ከፍተኛ ውጥረት ላይ ናት፤ የአጋዓዚ ጦር አካባቢዉን እየተቆጣጠረ ነዉ

በኢትዮጵያ የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነትና መብት ሳይከበር፤ አስከብሬያለሁ እያለ የቅጥፈት ዲስኩሩን በመንዛትና በብሄር ብሄረሰቦች ስም በመነገድ የአገዛዝ ዕድሜውን ለማርዘም ሌት ተቀን የሚባዝነው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በህዳር 29 በአሶሳ ከተማ ከየብሄር ብሄረሰቦቹ ቅጥረኛ ጄሌዎቹን በማሰባሰብ ለማስጨፈር ዝግጅት ይዞ በመንቀሳቀስ ላይ ሲሆን በእለቱ አገዛዙን ለመገርሰስ ጠበንጃ ያነሱ የነፃነት ሃይሎች ጥቃት ሊፈጽሙ ይችላሉ በሚል ስጋት በመኖሩ አካባቢው በወያኔ የአጋዚ ጦር ተከቦ ጥበቃ እየተደረገለት እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል። በዕለቱ ሊከሰት ይችላል ተብሎ ከተሰጋው ጥቃት ጋር በተያያዘ የአሶሳ ነዋሪዎች እንደልብ መዘዋወር በመከልከላቸው ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ወድቀው እንደሚገኙ ያደረሰን የአካባቢው ወኪል ዘጋቢያችን ከስጋቱ ጋር በተያያዘ በርካታ የወያኔ ቱባ ሹማምንቶች የጉዞ እቅዳቸውን መሰረዛቸው ታውቋል።

ብሄር ብሄረሰቦችን በመጨቆን እንዲሁም እኩይ ሴራዎችን በመፈብረክ እርስ በርስ በማጋጨት ለብዙ ሺህ ዜጎች በአሰቃቂ ሁኔታ መገዳደል ምክንያት የሆነው ፋሺስታዊው አገዛዝ በቤኒሻንጉል ክልል የሚገኙ ብሄር ብሄረሰቦችን ማለትም በርታ ፤ ጉሙዝ ፤ ሽናሻ ፤ ማኦ፣ ኮሞ ኦሮሞና አማራ የአገዛዙ እኩይ ሴራ ሰላባዎች በመሆናቸው የከፋ ስቃይ እየተፈራረቀባቸው እንደሚገኝ ይታወቃል። የፋሺስቱ ወያኔ አገዛዝ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንኳ በክልሉ በሚገኙ ገጠራማ አካባቢ የሚኖሩ ብሄር ብሄረሰቦችን ... ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ወያኔ ከፍተኛ የገንዘብ እጥረት ቀውስ ውስጥ ገባ፤ የአበዳሪዎችን በር እያንኳኳ ነዉ

በከፍተኛ የገንዘብ እጥረት የተመታው የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ስልጣኑን ለማስጠበቅ ሲል ከፍተኛ ብድር ለማጋበስ የአበዳሪ አካላትን ደጅ እየጠና እንደሚገኝ ታውቋል። አገሪቱ በኢኮኖሚ ረገድ አድጋለች፣ በምግብ ራሱዋን ችላለች፣ ሰላምና መረጋጋቱ አስተማማኝ ደረጃ ላይ ደርሷል በአጠቃላይ ሁሉም ነገር አልጋ ባልጋ እየሆነ መጥቷል የሚል የማወናበጃ የቅጥፈር ሪፖርቱን ራሱ እንዳዳቸው በሚፈነጭበት ቴሌቪዥን ሌት ተቀን የሚያስተጋባው የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በተደጋጋሚ በቴሌቪዥን መስኮቱ ከሚያቀርበውን ዘገባ ጋር የሚጣረዝ፤ ነገር ግን የፈጠጠውን የአገርቱ ነባራዊ ሃቅ የሚያሳይና አገዛዙ ሚስጥራዊ በሆነ መልኩ ለባለሃብቶች ያቀረበውን ሪፖርት ፋይናንሻል ታይምስ የተባለው አለማቀፍ የመገናኛ ብዙሃን ይፋ አድርጎታል።

ፋይናንሻል ታይምስ የተባለው አለማቀፍ የመገናኛ ብዙሃን ከአለማቀፍ የግል ባንኮች ሳይቀር ለመበደር ደጅ እየጠና የሚገኘው የጉጅሌው ወያኔ ለግል አበዳሪ ተቋማት ባለሃብቶች የሰጠውን ማስጠንቀቂያ ይፋ ማድረጉ የታወቀ ሲሆን አገዛዙ የውጭ ኢንቨርስተሮች ለኢትዮጵያ ብድር ከመፍቀዳቸው በፊት ሊያዉቋቸው ይገባል ያላቸው ነጥቦች ከፖለቲካ አለመረጋጋት፣ ከረሃብና ከጦርነት ጋር አያይዞ ማቅረቡ ታውቋል። አበዳሪ ባለሀብቶች ከኤርትራ ጋር ጦርነት እንደገና ሊያገረሽ እንደሚችል አስቀድመው ማወቅ አለባቸው ያለው እብሪተኛው ወያኔ፣ ከጅቡቲ ጋር ያለው ግንኙነት በሆነ መልኩ ቢሻክር ጅቡቲ ወደቡዋን ልትዘጋ የምትችልበት አጋጣሚ እንደሚኖርም ልብ ሊሉ ይገባል ሲል ያለበትን አጣብቂኝ ገልጿል። በተለይ መጪውን የይስሙላ ምርጫ ተከትሎ ግጭትና አለመረጋጋት በአገሪቱ ሊከሰት እንደሚችል ባለሃብቶች ከወዲሁ ማወቅ እንዳለባቸው አሳስቧል።

በተጨማሪም በአገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ ረሃብ ሊነሳ የሚችልበት አደጋ አንዣቦ እንደሚገኝ ያወሳው የአገዛዙ ሪፖርት በመላ አገሪቱ ከፍተኛ የሆነ ድህነት ከመንሰራፋቱም በላይ በአገሪቱ የመጠባበቂያ ገንዘብ እያሰቆለቆለ በመሄዱ፤ በአሁኑ ሰአት አገሪቱ ለሁለት ወር ብቻ የሚበቃ የመጠባበቂያ ገንዘብ እንዳላትም ይፋ አድርጓል።

አድማጮቻችን የሪፖርቱን ይፋ መደረግ ተከትሎ ኢትዮጵያውያን አስተያየታቸውን እየሰነዘሩ ሲሆን የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ከገንዘብ እጦቱ ጋር በተያያዘ በተለይ ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ በማጋበስ የአገዛዝ ዘመኑን ለማርዘም የጀመራቸው የተለያዩ ፕሮጀክቶች አደጋ ተጋርጦባቸው እንደሚገኝ ተነግሯል። የጉጅሌው ወያኔ ፕሮጀክቶቹን ህዝቡን በመደለል ስልጣን ላይ ለመቆየት የሚጠቀምባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ የህወሓት ቱባ ሹማምንቶች ከፍተኛ ገንዘብ የሚዘርፉባቸው ሲሆን በገንዘብ እጦት የፕሮጀክቶቹ መቋረጥ በአገዛዙ ላይ ሌላ አደጋ ሊፈጥርበት እንደሚችልም ተመልክቷል። ... ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## የህወሃት ምርጫ የህዝብ መከራ!

ህወሃቶች እኛ ከሌለን ይህችን አገር እንበትናታለን፤ ይህችን አገር የምንሰብር እኛ የምንጠግን እኛ እያሉ እንደሚያሚርቱ ሰምተናል። እኛ የቀረፅነው ፖሊስ ከሚቀየር ሞታችንን እንመርጣለን እያሉ ማቅራራታቸውም ከህዝብ የተሰወረ ነገር አይደለም። የህወሃት ፖሊሲ የሚቀየረው በመቃብርችን ላይ ነው የሚል የማይናወፅ አቋማቸው መቼም ቢሆን በሠለጠነ መንገድ በውይይትና በድርድር እንደማይቀየር ደጋግመው አሳይተውናል። ህወሃቶችን በሠለጠነ መንገድ ተደራድሮ እና ሰጥቶ በመቀበል መርህ ለለውጥ አዘጋጃለሁ ማለት ከእባብ የእርግብ እንቁላል እንደመመኘት ያህል ነው። ከእባብ የእርግብን ዘር የሚጠብቅ ማን ነው?

እንግዲህ ህወሃቶች ይህን የመሰለ የከረረ አቋም ይዘው ምርጫ ለምን ያደርጋሉ ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይሆናል። ይሄ ህወሃቶች ለኢትዮጵያና ለህዝቧ ራዕይ የሌላቸው ከመሆን የሚመነጭ ነው። ድርጅቱ ራዕይ አልባ የሆነው ደግሞ በህወሃት ውስጥ የተሰባሰቡ ግለሰቦች ራዕይ አልባ በመሆናቸው ነው። ህወሃቶች የሚኖሩለትም ሆነ የሚሞቱለት ቁም ነገር ከመብልና መጠጥ የዘለለ አይደለም። ህወሃቶች ራዕይ ቢኖራቸው ኑሮ በታሪክ የሚያስወቅሳቸውንና የህዝቡን ፍቅር የሚያሳጣቸውን እኩይ ተግባራት ባልፈፀሙ ነበር። ራዕይ የሌላቸው በመሆኑ ለሚፈፅሙት ወንጀል ሁሉ ገደብ እንዳይኖራቸው ሆኑ። ራዕይ ያለው ሰውም ሆነ ድርጅት እኔ ብቻ አይልም። ራዕይ የሰነቀ ድርጅትም ሆነ ሰው ከራሱ ክበብ አልፎ ሌላው እንደምን ሁኖ በሠላም እና በደስታ እንደሚኖር ያስባል እንጂ ዕለት ዕለት ደም በማፍሰስ አይኖርም።

ህወሃት በምርጫ ስልጣኑን እንደማይለቅ ለራሱ የማለ ድርጅት ነው። እዚህ መሃላ ላይ ያደረሰው ደግሞ እስከ ዛሬ የፈፀማቸው ወንጀሎቹ ናቸው። የጨበጠውን ስልጣን በምርጫ ቢለቅ ነገ የሚከተለውን ጠንቅቆ ያውቃል። ትላንት ያፈሰሱት የንፁሃን ደም ከኢትዮጵያ ምድር ላይ እየጮኸ ነው። ዘርፈው የገነቡት ህንፃ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ ቆመው ሌብነታቸውን እየመሰከሩባቸው ነው። በልማት ሥም ከኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ተዘርፎ የተደራጀው የንግድ ተቋም በኢትዮጵያ ህዝብ ወዝና ደም ታጥኖ እንዳማረበት አለ። ህወሃት የኢትዮጵያ የህዝብ ጠላት ሆኖ ራሱን ያቆመ ቡድን በመሆኑ በሰላማዊ እና በሰለጠን መንገድ የያዘውን ሥልጣን ለህዝብ አይለቅም።

እንግዲህ ምን ይሻላል ?

ህወሃቶች ኑና እንወዳደር ብለዋል። እነዚህ ቡድኖች ኑና እንወዳደር ሲሉ እነርሱ የብረት ቦክስ ጨብጠው፤ ሌሎቹ ደግሞ ሌጣቸውን ሁነው ያለ በቂ ታዛቢ እንዲፎካከሯቸው ወስነው ነው።እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ሁነንም ቢሆን የምንወዳደረው ለነፃነት መሆን ይኖርበታል። ከነፃነት በመለስ ያለው ማንኛውም ዓይነት የምርጫ ውጤት በአገራችን እየተካሄደ ያለውን ዝሪፊያ፤ ዘረኝነት፤ እሥራት እና ግድያ ያስቆማል የሚል ዕምነት በማንም ዘንድ ያለ አይመስለንም። በምርጫ ውድድር የምናተርፈው የህግ የበላይነት፤ እኩልነት እና ነፃነት ካልሆነ ተጎጂው ሰፊው ህዝብ ይሆናል።

ህወሃት የብረት ቦክስ ጨብጦ እኛ ደግሞ ሌጣችንን ሁነን መወዳደር ፍትሃዊ አይደለም በማለት ድምፃቸውን እያሰሙ ያሉት ወገኖችም የህዝብን መሠረታዊ ፍላጎት ለሟሟላት አስፈላጊ የሆነው ነፃነት ዋነኛው ግባቸው መሆን ስለሚኖርበት ይመስለናል። ወደ ውድድር ከመግባታችን በፊት ህወሃት የብረት ቦክሱን ያውልቅ፤ የመወዳደሪያ መድረኩም እኩል ይሁን ማለታቸው የሚሰማ ቢኖር ፍትሃዊ ጥያቄ ነው። የህወሃትን የብረት ቦክስ ለማስወለቅ መሥዋዕትነት ለመክፈል መዘጋጀታቸውም ለነፃነት የሚከፈል ዋጋ ይሆናል። ከህወሃት ጭካኔና ድንቁርና ስንነሳ በዚህ መንገድ የሚሄዱት የሚከፍሉት መሥዋዕትነት ከባድ እንደሚሆን እንጠብቃለን። ግን ደግሞ ነፃነት ያለ መሥዋዕትነት እንደማይገኝ ሌላው ቀርቶ ነፃነትን የማያውቁት ህወሃቶች ያውቃሉ። በማንኛውም መልኩ ከህወሃቶች ጋር አገት ለአንገት ተናንቀው በአገር ቤት ውስጥ እየተንቀሳቀሱ ያሉት ድርጅቶች ልበ ሙሉነታቸውን እጅግ አድርገን እናደንቃለን። እምቢ ለነፃነቴ፤ እምቢ ለክብሬ፤ እምቢ ለህወሃቶች ቀይ መስመር ማለት ይሄ እንጂ ሌላ አይደለም። እንግዲህ ዘረኞቹና ዘራፊዎቹ ቡድኖች ሊያደርሱ የሚችሉትን ጉዳት መቀነስ የሚቻልበትን መንገድ ማሰብ ተገቢ ይሆናል። ህዝቡ በልዩ ልዩ ሰንሰለት የታሠረ በመሆኑም በሚፈለገው መጠን ወጥቶ የትግሉ አካል ካልሆነም ተስፋ መቁረጥ አይገባም።በተጀመረው ላይ ይበልጥ እያጠናከሩና እየጨመሩ እየተካሄደ ያለውን ትግል መቀጠል ምርጫ የሌለው ሥራ ነው።

ግንቦት ሰባት የፍትህ የነፃነትና  የዲሞክራሲ ንቅናቄ አገር ቤት ሁነው ከጭካኔ በቀር ሌላ ዕውቀት ከሌላቸው ህወሃቶች ጋር በትግል ላይ ያሉ ድርጅቶችን ያደንቃል። ያመስግንማል። በርቱ ከማለት በቀር የምንለው ሌላ የለንም።

እኛ የጀመርነውን ሁለ ግብ ትግል እያጠናከርነው ነው።የአገራችንን ውርደት፤ የወገኖቻችንን ጉስቁልና እያየን ዝም ብንል እርግማን ይሁንብን ያሉ ወጣቶች የአያቶቻቸውን ጋሻና ጦር አንስተዋል። እናቶችም ልጆቻቸውን መርቀው ፋኖ ተሠማራ ብለዋል። ሌሎች ደግሞ የኋላ ደጀን ሁነው ሳያቅማሙ ቁመዋል። ብዙ ባለሙያዎች ለአገራቸው የሚከፈልውን መሥዋዕትነት ለመክፈል ተዘጋጅተዋል።

እንግዲህ የጀመርነውን ትግል የሚያስቆመን ምድራዊ ኃይል የለም። የህወሃት የመረጃ መረብ ይበጣጠሳል። የጦር ኃይሉ ከጥቂት ዘረኞችና ሌቦች ይልቅ ወገኑን እንደሚመርጥ በየቀኑ የሚደርሱን መረጃዎች ያሳዩናል። የከተማው ህዝብ ህወሃቶችን አክ እንትፍ ካላቸው ብዙ ዘመን ሁኖታል። የገጠሩም ህዝብ የህወሃት ዋሻ የመሆኑ ነገር አብቅቷል። ይሄ ሁሉ የእኛ አቅማችን ነው። ይሄን አቅም አደራጅተንና ሥራ አሲይዘን አገራችንን ነፃ የምናወጣበት ግዜ ሩቅ አይደለም።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !**

---

## ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ህጋዊ ተቃዋሚዎችን አክራሪ ናቸዉ በሚል ሊመታቸዉ ማሰቡ ተሰማ

በኢትዮጵያ ህገ መንግስት አንቀጽ 31 መሰረት በህጋዊ መልኩ ተመዝግበው ሰላማዊ የፖለቲካ እንቃስቃሴ የሚያደርጉ ተቀናቃኝ ፓርቲዎችን በሽብርተኝነት እና ጽንፈኝነት በመፈረጅ የጥቃት ኢላማ ለማድረግ መታሰቡን የዝግጅት ክፍላችን የፌደራል መንግስት የጸጥታ ጉዳዮች ሰሞኑን ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር ካካሄደው ውይይት ለመረዳት ተችሎአል፡፡

የትግራይ፣ቤንሻንጉል ጉሙዝና አማራ ክልል ሃላፊዎች ሰማያዊ ፣አንድነትና መኢአድ ፓርቲዎች ጽንፈኞች በመሆናቸው በአክራሪነት ሲሳተፉ የነበሩ ወጣቶችን በማሰባሰብ ለሽብር እያዘጋጁ ነው በማለት የገዢውን መንግስት ፖሊሲዎች በሰላማዊ መንገድ የሚቃዎሙትን ፓርቲዎችን በወንጀለኛነት ሲፈርጁ ተደምጠዋል፡፡መልካም ተሞክሮ ነው በማለት በየክልሉ አስተዳደርና ጸጥታ ጉዳዮች ኃላፊዎች የቀረበው ሪፖርትና የወደፊት እንቅስቃሴ በመጭው ምርጫ 2007 የተፈረጁት ፓርቲዎች የህዝብ ድምጽ በማግኘት የገዢው መንግስት ስጋት እንዳይሆኑ ከማሰብ የተነሳ መሆኑን የውስጥ ምንጮች ለኢሳት ገልጸዋል፡፡በሃገሪቱ በትጋት ከሚንቀሳቀሱና የህዝብ ድጋፍ በብዛት እያገኙ ከመጡት የተቀናቃኝ ፓርቲዎች መካከል የሚመደበው የሰማያዊ ፓርቲን እንቅስቃሴ ለማስቆም እና የምርጫ 2007 ስጋት መሆናቸውን ለማከተም ገዢው መንግስት በየአካባቢው የሚከሰቱ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎችን በሙሉ ከተቀናቃኝ ፓርቲዎች ጋር ማገናኘት መጀመሩ ሆን ተብሎ ሰላማዊ ተቃዋሚዎችን ለመምታት የተዘጋጀ መሆኑን ምንጮች ጠቅሰዋል።

## አሰሳ ከፍተኛ ውጥረት ላይ ናት፤ የአጋዓዚ  ጦር

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በግፍ ያለምንም ተተከ ቦታና የካሳ ክፍያ ከቀያቸው በማፈናቀል ቦታዎቻቸውን የአገዛዙ ቱባ ሹማምንቶችና ለሹማንቱ ቅርበት ያላቸው ባለሃብቶች በመቀራመት ነዋሪዎችን ለከፋ እንግልት መዳረጋቸው መዘገቡ አይዘነጋም። በክልሉ ተወልደው ያደጉና ለዘመናት ኑሮዋቸውን በአካባቢው ያደረጉ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ የአማራ ብሄር ተወላጆች በግፍ መፈናቀላቸውንና አካባቢውን ለቀው እንዲወጡ መደረጋቸውም ይታወሳል።

በተያያዘ ዜና የአገር ሃብትን በመዝረፍና በመመዝበር ወደር ያልተገኘለት ፋሽስቱ ወያኔ የብሄር ብሄረሰቦችን ቀን ለማክበር በሚል ከ 300 ሚሊዮን ብር በላይ የአገር ሐብት በየ አመቱ እያወደመ እንደሚገኝ ታውቋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ከዝግጅቱ ጋር በተያያዘ በየ አመቱ ወጭ የሚደረገውን የአገር ሐብት የጉጅሌው ቱባ  ሹማምንቶች ጋር ቅርበት ያላቸው ድርጅቶች የአዘጋጅነት ሚናውን በመውሰድና የተለያዩ ስራዎችን በማከናዎን ገንዘቡን ከቱባ ሹማምንቱ ጋር እየተከፋፈሉት እንደሚገኙ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ከዚህ ዘረፋ ጋር ተያይዞ ቀላል የማይባሉ የአገዛዙ ቱባ ሹማምንቶች በሐብት ረገድ እየደለቡበት ለማወቅ ችለናል።

# ብሄራዊ ብድር የዕድገታችን ምንጭ እንጂ የደኅንነታችን ስጋት ሊሆን አይገባም

እኛ ሰዎች ሁሌም ከምንፈራዉና ከምንጠላዉ አንዴ ከገባንበት ደግሞ የቱንም ያክል ብንጠላዉና ብንፈራዉ እየደጋገምን የምንዘፈቅበትና በቀላሉ የማንወጣዉ አዘቅት ቢኖር ብድር ወይም የብድር ልጅ የሆነዉ ዕዳ ነዉ። ብድር ግለሰቦች ብቻ ሳይሆኑ የንግድ ድርጅቶች፤ ማዘጋጃ ቤቶች፤ ትላልቅ ኮርፖሬሺኖችና አገሮች በአጭርና በረጂም ግዜ የሚያጋጥማቸዉን የገንዘብ እጥረት የሚሸፍኑበት መንገድ ነዉ። ወይም ቀለል ባለ አማርኛ ብድር ወደፊት በምናገኘዉ ገቢ ዛሬን መኖር ማለት ነዉ። ብድር ግለሰቦች፤ ድርጅቶች ወይም አገሮች የመክፈል አቅማቸዉን እያዩ ቢበደሩና የተበደሩትን ገንዝብ ዉጤታማ በሆነ መንገድ ከተጠቀሙበት የእድገትና የብልጽግና መንገድ የሚከፍት አለዚያም የምንበደረዉ ብድር ከአቅም በላይ ከሆነና ዉጤታማ ባልሆነ መልኩ ከተጠቀምንበት ደግሞ በቀላሉ የማንወጣዉ መቀመቅ ዉስጥ ይዞን የሚገባና ጫናዉ ከትዉልድ ወደ ትዉልድ የሚተላለፍ ዕዳ ነዉ። ዕዳ ደግሞ በተለይ አገሮች የሚገቡበት ዕዳ ተከፍሎ ካላለቀ ወይም በምህረት ካልተሻረ በቀር ወለዱ ወለድ እየወለደ በተበዳሪ አገሮች የኤኮኖሚ እድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያደርግ የዕድገትና የብልፅግና ጠላት ነዉ። ዛሬ ሰፋ አድርገን የምንመለከተዉ ብድርና ዕዳን ቢሆንም ዋናዉ ትኩረታችን ግን አገራችን ኢትዮጵያን ጨምሮ በታዳጊ አገሮች የኤኮኖሚ ዕድገት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚያደርገዉን ብሄራዊ ብድርና ዕዳ ነዉ። ሁላችንም እንደምናዉቀዉ አገራችን ኢትዮጵያ ባለፉት ሃያ አመታት በብድር ላይ ብድር እየተበደረች አንዱንም ሳትከፍል በድጋሚ እየተበደረች ከድጡ ወደማጡ እየገባች ነዉ።

የኢትዮጵያ መንግስት መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ የዉጭ አገር ምንጮች ብድር መበደር ከጀመረ ብዙ አመታት ተቆጥረዋል።ከቀዳማዊ ሚኒልክ በኋላ ኢትዮጵያን ለረጂም አመታት የመሩት ሦስቱ መንግስታት የብድር ጥማት ከፍተኛ ቢሆንም በብድር መጠኑም ሆነ በተከማቸ የዕዳ መጠኑ ዛሬ በስልጣን ላይ እንዳለዉ እንደ ወያኔ አገዛዝ የአገራችንን ብሄራዊ ደህንነት ለአደጋ ባጋለጠ መልኩ ብድር የተበደረና ዕዳ ዉስጥ የተዘፈቀ አገዛዝ ኢትዮጵያ አይታ አታዉቅም። የወያኔ አገዛዝ አገር ዉስጥ ቦንድ እየሸጠና ብሔራዊ ባንክን እያስገደ በተለያየ መልኩ የሚወስደዉ ብድር ከአለም ባንክ፤ ከአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት፤ ከዉጭ አገር ባንኮችና አበዳሪ አገሮች በየአመቱ ከሚበደረዉ ብድር ጋር ተደምሮ የዛሬዉን ኢትዮጵያዊ ብቻ ሳይሆን የዛሬዉን ኢትዮጵያዊ የልጅ ልጆች ጭምር ባለዕዳ አድርጓቸዋል።

የወያኔ አገዛዝ ለህዳሴዉ ግድብና ለእድገትና ትራንስፎርሜሺን ዕቅድ ማስፈጸሚያ በሚል የአገሪቱን አመታዊ ገቢና የመክፈል አቅም በላገናዘበ መልኩ እጅግ በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ ገንዝብ ከተለያዩ የአገር ዉስጥና የዉጭ አገር ምንጮች እየተበደረ ነዉ። ይህ መጠነ ሰፊ ብድር በረጂም አመት የሚከፈልና ከፍተኛ ወለድ የተሸከመ ሲሆን ወያኔ ይህ ብዙ ኢትዮጵያዉያንን ያሰጨነቀ ብሄራዊ ዕዳ አልበቃ ብሎት ከአቅም ዉጭ የጀመራቸዉን ፕሮጀክቶች ለማስጨረስ ነዉ በሚል ሰበብ አሁንም አገራችን ኢትዮጵያን ከዕዳ ወደ ዕዳ እየከተታት ይገኛል። በተለይ ወያኔ አበዳሪ አገሮች፤ የአለም ባንክና ወዳጆቹ የሆኑ መንግስታት ጭምር ተዉ ይቅርብህ ብለዉ እየመከሩት አልሰማ ብሎ በዚህ አመት ለመሸጥ ያሰበዉ ሉዓላዊ ቦንድ ወይም ፈረንጆቹ ሶቨርን ቦንድ ብለዉ የሚጠሩት ቦንድ ሽያጭ የጉዳዩ አሳሳቢነት የገባቸዉን ኢትዮጵያዉያንንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ከወዲሁ እያሰጨነቀ ነዉ። በእርግጥም ሉዓላዊ ቦንድ ሽያጭ የሚያስጨንቅ ብቻ ሳይሆን አንደ ኢትዮጵያ አይነቶቹን ቀድሞዉኑም ዕዳ ዉስጥ የተዘፈቁ ደሃ አገሮች ህልዉና አደጋ ዉስጥ የሚከት የኤኮኖሚ ዕድገትን ብቻ ሳይሆን የአገር ደህንነትን ጭምር የሚፈታተን አደገኛ ጅምር ነዉ። ለመሆኑ ሉዓላዊ ቦንድ ምንድነዉ? አደገኛነቱስ ምኑ ላይ ነዉ?

ሉዓላዊ ቦንድ አገራቸዉ ዉስጥ ዝቅተኛ ቁጠባ የሚታይባቸዉ ብሔራዊ መንግስታት አገራቸዉ ዉስጥ ከአቅማቸዉ በላይ የሆነ  የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥማቸዉ የሽያጭ ዋጋዉ በአገራቸዉ ገንዘብ ሳይሆን ያወጣናል ብለዉ በሚያምኑት በሌላ አገር ገንዘብ ለምሳሌ በዶላር ወይም በዩሮ የተተመነ ቦንድ እየሸጡ  ገንዝብ የሚበደሩበት መንገድ ነዉ። የየአገሩ መንግስታት ቦንድ አየሸጡ ገንዘብ መበደራቸዉ አዲስ ክስተት አይደለም፤ ሆኖም መንግስታት በተለይ የታዳጊ አገሮች መንግስታት ቦንድ የሚሸጡት አገራቸዉ ዉስጥ በአገራቸዉ ገንዘብ ነዉ። ሉዓላዊ ቦንድን ልዩ የሚያደርገዉ ቦንዱ የሚሸጠዉ በአለም አቀፍ ደረጃ ሆኖ ሽያጩ የሚከናወነዉ ደግሞ በዉጭ ምንዛሪ መሆኑ ነዉ። ሉዓላዊ ቦንድ ሽያጭን ከመደበኛ ቦንድ ሽያጭ የሚለዩት ብዙ ነገሮች አሉ።

ሉዓላዊ ቦንድ ከሌሎች መደበኛ ቦንዶች ጋር ሲነፃፀር ብዙ ዉስብስብ ችግሮች አሉበት። ለምሳሌ ሉዓላዊ ቦንድ የሚገዙ አገሮች ወይም ድርጅቶች ቦንዱን የሚገዙት በዉጭ ምንዛሪ ነዉ፤ ሁለተኛ ሻጩ አገር ለቦንዱ የሚከፍለዉ ወለድ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነዉ። በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ብዙዉን ግዜ ሉዓላዊ ቦንድ የሚሸጥ አገር ከቦንዱ ሽያጭ የሚያገኘዉ ገንዝብ ወለዱ የተቀነሰለት ገንዝብ ነዉ። ለምሳሌ በ10 በመቶ ወለድ የአንድ መቶ ሚሊዮን ዶላር ሉዓላዊ ቦንድ የሚሸጥ አገር እጁ ላይ የሚገባዉ ዘጠና ሚሊዮን ዶላር ሲሆን ብድሩን መልሶ ሲከፍል የሚከፍለዉ ደግሞ አንድ መቶ ሚሊዮን ዶላር ነዉ። ይህ ማለት ደግሞ ቦንድ ሻጩ አገር ወለዱን የሚከፍለዉ በተበደረዉ ገንዝብ ተጠቅምበት ሳይሆን የተበደረዉ ገንዘብ ገና እጁ ላይ ሳይገባ ነዉ ወለዱን የሚከፍለዉ። ለሉዓላዊ ቦንድ የሚከፈለዉ ወለድ እጅግ በጣም ከፍተኛ ስለሆን ብዙ አገሮች በተለይ ታዳጊ አገሮች ሉዓላዊ ቦንድ መሸጥ የማይፈልጉት ይህንኑ ለብድሩ የሚከፈለዉን ከፍተኛ ወለድ ሰለሚፈሩ ነዉ።

የወያኔ አገዛዝ እንደተራ ወረቀት እየፈበረከ ገበያ ዉስጥ የሚበትነዉ ገንዘብና ከአገር ዉስጥ ባንኮች ከአቅሙ በላይ የሚበደረዉ ገንዝብ ኢትዮጵያ ዉስጥ የዋጋ ንረቱን ምን ያህል ሰማይ  ላይ እንደሰቀለዉና የኢትዮጵያን ህዝብ ምን ያክል እንዳደኸየ ሁላችንም በግልጽ የምናዉቀዉ ሀቅ ነዉ። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ የአገራችን ገበሬና ሠራተኛ የወያኔ ብልሹ የኤኮኖሚ ፖሊሲ ለአመታት ከፈጠረዉ የዋጋ ንረት በሽታ ሳይድን ነዉ ሌላ ሉዓላዊ ቦንድ የሚባል በቀላሉ የማይድን አደገኛ በሽታ ፊቱ ላይ የተደቀነበት።

ሉዓላዊ ቦንድ ደሃ አገሮች የሚሸጡትና ኃብታም አገሮች የሚሸጡት እየተባለ በሁለት ይከፈላል። ኃብታም አገሮች የሚሸጡትን ቦንድ ከነወለዱ ከፍለዉ ይጨርሳሉ ተብሎ በቦንድ ገዢ አገሮችና ድርጅቶችና ስለሚታመን እነዚህ አገሮች ለሚሸጡት ሉዓላዊ ቦንድ የሚከፍሉት ወለድ ዝቅተኛ ነዉ። ኢትዮጵያን መሰል ደሃ አገሮች ግን ብድር የመክፈል ችሎታቸዉ አስተማማኝ ስላልሆነ ሉዓላዊ ቦንድ ሲሸጡ ለቦንድ ገዢዉ የሚከፍሉት ወለድ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነዉ። ስለሆነም ደሃ አገሮች በተለይም እንደ ኢትዮጵያ አይነቶቹ ለመጀመሪያ ግዜ ሉዓላዊ ቦንድ ለሚሸጡ አገሮች ቦንድ ለመሸጥ ከመወሰናቸዉ በፊት ማስተካከል ያለባቸዉ ብዙ ነገሮች አሉ። በነገራችን ላይ ሉዓላዊ ቦንድ መሸጥ በራሱ ምንም ጥፋት የለበትም። እንዲያዉም ህዝባዊና አገራዊ ሃላፊነት የሚሰማቸዉ መንግስታት ሉዓላዊ ቦንድ በመሸጥ የፋይናንስ ጉድለታቸዉን በመሸፈን  የአገራቸዉን እድገት አቅጣጫ ቀይሰዉ ጠንካራ ኤኮኖሚ የመገንባት አቅም  ማግኘት ይችላሉ። በኛም አገር ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎቸ አንደኛ አገራዊ ሃላፊነት ቢሰማቸዉ፤ ሁለተኛ በአቅማቸዉ ቢኖሩ፤ ሦስተኛ በአገር ስም የተበደሩትን ገንዘብ መዝረፍ አቁመዉ ሁሉንም ለአገር ጥቅም ቢያዉሉትና ተበድረዉ በሚሰሯቸዉ ፕሮጀክቶች ሁሉም ኢትዮጵያዊ እኩል ተጠቃሚ ቢሆን አገራችን መደበኛ ቦንድም ሆነ ሉዓላዊ ቦንድ በመሸጥ የምትበደረዉ ገንዘብ ብሄራዊ አቅም ስለሚገነባ ዕዳዉ ብዙም አያስፈራንም። ችግሩ ያለዉ ሉዓላዊ ቦንድ መሸጡ ላይ ሳይሆን እዚህ ዉሳኔ ላይ ከመደረሱ በፊት መወሰድ ያለባቸዉን እርምጃዎች በጥንቃቄ መዉሰዱ ላይ ነዉ። የወያኔም ትልቁ ችግር ያለዉ እዚህ ላይ ነዉ። የቦንዱ ሽያጭ ይዞት የሚመጣዉን ጣጣና ፈንጣጣ ግምት ዉስጥ ሳያስገባ ነዉ ሉዓላዊ ቦንድ እሸጣለሁ ብሎ ያወጀዉ።

የወያኔ አገዛዝ የበጀት ዲሲፕሊን የሌለዉ፤ በአቅሙ የማይኖር፤ እመራዋለሁ የሚለዉን አገር ኃብት የሚዘርፍና በሚያደርጋቸዉ ነገሮች ሁሉ ኢትዮጵያን የማያስቀድም የአገርና የህዘብ ጠንቅ የሆነ ክፉ አገዛዝ ነዉ።ኢትዮጵያን ጨምሮ በመላዉ አለም የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን የወያኔ ፓርላማ የሉዓላዊ ቦንድ ሽያጭ ረቂቅ ህግ አፀደቀ ሲባል ቀልባቸዉ የረገፈዉ ከላይ የተጠቀሱትን የወያኔ ጠባዮች በሚገባ ሰለሚያዉቁ ነዉ። ወያኔ ከአገር ዉስጥም ሆነ ከአገር ዉጭ የብድር ምንጮች በሚበደረዉ ገንዘብ መንገድ፤ ህንፃና ግድብ ሊሰራ ይችላል። እነዚህ ነገሮች በመሰራታቸዉ የሚከፋ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለንም። ብዙ ኢትዮጵያዉያንን የሚከፋቸዉ ወያኔ በነሱ ስም በተበደረዉ ብድር በጀመራቸዉ ፕሮጀክቶች ሁሉ መጠቀም አለመቻላቸዉና በገዛ አገራቸዉ የበይ ተመልካች መሆናቸዉ ነዉ። እዚህ ላይ የህዳሴዉን ግድብ አንደ ምሳሌ ወስደን መመልከት እንችላለን። የህዳሴዉን ግድብ የእንጂኔሪንግ ኮንትራት ያለምንም ጨረታ አሸንፎ ከፍተኛ ትርፍ የሚያጋብሰዉ መስፍን ኢንጂኔሪንግ የተባለ የወያኔ ድርጅት ነዉ። ለህዳሴዉ ግድብ ማሰሪያ ሲሚንቶ የሚያቀርበዉ የወያኔዉ መሶብ ሲሚንቶ ፋብሪካ ነዉ። ለግድቡ ፕሮጀክት የትራንስፖርትና ማጓጓዣ አገልግሎት የሚሰጡት የአዜብ መስፍን ዘመዶች ናቸዉ;፡ ለህዳሴዉ ግድብ ሰራተኞች የምግብ አገልግሎት የሚሰጡት የወያኔ ኩባንያዎች ናቸዉ። የህዳሴዉን ግድብ እንደምሳሌ ወሰድነዉ እንጂ ኢትዮጵያ ዉስጥ በብድርም ሆነ በእርዳታ ገንዘብ በሚሰሩ ፕሮጀክቶች ሁሉ ተጠቃሚዉ ወያኔና ባለ ሟሎቹ ናቸዉ። ወያኔ እንደ ተራራ የቆለለዉን ብድር እስከነወለዱ የሚከፍለዉ ግን የኢትዮጵያ ህዝብ ነዉ።

የአለም ባንክንና አለም አቀፉን የገንዝብ ድርጅት ጨምሮ ብዙ የኤኮኖሚ ሳይንስ ጠበብቶች አገሮች በተለይ የዉጭ ዕርዳታ ጥገኛ የሆኑ ደሃ አገሮች ሉዓላዊ ቦንድን አገር ዉስጥ ለሚያጋጥማቸዉ የገንዝብ ጉድለት ማሟያ አድረገዉ እንዳይጠቀሙ በተከታታይ ያስጠነቅቃሉ። የወያኔ አገዛዝም ይህ ማስጠንቀቂያ በተከታታይ ከደረሳቸዉ መንግስታት አንዱ ነዉ። ... ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ወያኔ ከፍተኛ የገንዘብ እጥረት ቀውስ ውስጥ ገባ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ስራዎቹ ከተስተጓጓሉ በዘረፋና በጥቅም የተሳሰሩት የአገዛዙ ቱባ ሹማምንቶችና ቅልብ ካድሬዎች ያለምንም ጥያቄ አገዛዙን የመከዳታቸው አይቀሬነት አጠያያቂ እንደማይሆን በስፋት እየተነገረ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል።

ባለሀብቶች ከኤርትራ ጋር ጦርነት እንደገና ሊያገረሽ እንደሚችል አስቀድመው ማወቅ አለባቸው ያለው መንግስት፣ ከጅቡቲ ጋር ያለው ግንኙነት በሆነ ቢሻክር ጅቡቲ ወደቡዋን ልትዘጋ የምትችለበት አጋጣሚ እንደሚኖርም ልብ ሊሉ ይገባል ብሎአል። በተለይ መጪውን ምርጫ ተከትሎ መንግስት ምርጫው በሰላም ይጠናቀቃል ብሎ ቢያስብም፣ ግጭትና አለመረጋጋት ሊከሰት እንደሚችል ባለሃብቶች ከወዲሁ ማወቅ እንዳለባቸው አሳስቧል።

በአገሪቱ ውስጥ ረሃብ ሊነሳ የሚችልበት አደጋ አለ ያለው የኢህአዴግ መንግስት፣ ከፍተኛ የሆነ ድህነት እንዳለም ሊያዉቁት እንደሚገባ አሳስቧል። በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰው ልማት መስፈረት ኢትዮጵያ ከ187 አገራት በመጨረሻዎቹ ተርታ ከሚገኙት አገራት በ173ኛ ደረጃ ላይ እንደምትገኝ አበዳሪዎች ሊያዉቁት እንደሚገባ አስጠንቅቆ፣ መንግስት ከፍተኛ ሆነ የገንዘብ እጥረት እንዳጋጠመውም አልሸሸገም። በተለይ የአገሪቱ የመጠባበቂያ ገንዘብ ( hard currency reserve) እያስቆለቆለ በመሄዱ፣ በአሁኑ ሰአት አገሪቱ ለሁለት ወር ብቻ የሚበቃ የመጠበባቂያ ገንዘብ እንዳላትም ይፋ አድርጓል።

መንግስት በሪፖርቱ ከቻይና ጋር ስላለው ግንኙነትም ይፋ አድርጓል። በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚካሄዱት ግንባታዎች ቻይና ወነኛዋ አበዳሪ አገር መሆኑዋን መንግስት ገልጾ፣ አምና ከውጭ ከተገኘው ብድር ውስጥ 69 በመቶው፣ በተመሳሳይ ሁኔታ ዘንድሮ ከተገኘው ብድር ውስጥ 42 በመቶው የቻይና መሆኑን ጠቅሷል። ዜድ ቲኢ፣ ሃዊይ እና የቻይና ኤልክትሪክ ኩባንያ ባለፉት ጥቂት አመታት 2 ቢሊዮን ዶላር ብድር ለኢትዮጵያ በመስጠት ስራውን እርሳቸው እየሰሩ መሆኑን ዘገባው አመልክቷል።

አበዳሪ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚገጥማቸው ነገር ማስጠንቀቂያ በግልጽ ቢሰጣቸውም፣ ለኢትዮጵያ የ1 ቢሊዮዮን ዶላር ብድር ለመፍቀድ ፍላጎት ማሳየታቸውን ጋዜጣው ዘግቧል። ይህም የሆነበት ምክንያት የአሜሪካ፣ የእንግሊዝ፣ የአውሮፓ ህብረትና የጃፓን ቱጃሮችና ኩባንያዎች በእነዚህ አገራት ባንኮች ገንዘባቸውን በማስቀመጥ የሚያገኙት ወለድ እጅግ አነስተኛ መሆን፣ የመክሰር አደጋ ላለባቸው አገሮች በድፍረት በማበደር እድላቸውን ለመሞከር መፈለጋቸውን ጋዜጣው ዘግቧል። በገንዘብ ኢኮኖሚ ላይ በሚሰጡት አስተያየት የሚታወቁት ፕ/ር ሰኢድ ሃሰን የምእራብ አገራት ባለሃብቶች ከባንኮች የሚያገኙት ወለድ ወደ ዜሮ እየተጠጋ መምጣቱ ብድሩን ለመፍቀድ ሳይገፋፋቸው እንዳልቀረ ለኢሳት በኢሜል በመግለጽ የፋይናንሻል ታይምስን አስተያየት አጠናክረዋል።

መንግስት በአገር ውስጥ ሁሉም ጥሩ እንደሆነ እየተናገረ በድብቅ እንዲህ አይነቱን አስደንጋጭ ሪፖርት ለምን ለማውጣት ፈለገ የተባሉት ፕ/ር ሰኢድ፣ የተለያዩ መላ ምቶችን አቅረበዋል። መንግስት የውጭ አማካሪ ድርጅቶችን በመቅጠር ሪፖርቱን ሳያዘጋጅ እንዳልቀረ የተናገሩት ፕሮፌሰሩ፣ የውጭ አማካሪ ድርጀቶች ደግሞ እያንዳንዷን ችግር በግልጽና ተአማኒነት ባለው ሁኔታ የማቅረብ ግዴታ ስላለባቸው ሪፖርቱን በዚህ መልክ አቅረበውት ሊሆን ይችላል ብለዋል።

## ብሄራዊ ብድር የዕድገታችን ምንጭ እንጂ የደኅንነታችን ስጋት

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

ሆኖም የማንንም ምክር የማይሰማዉ ወያኔ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ሉዓላዊ ቦንድ በመሸጥ መዘዙ ከትዉልድ ወደ ትዉልድ የሚተላለፍ ክፉ በሽታ እየዘራ ይገኛል። ወያኔ እስከዛሬ የተበደረዉ ብድር ምኑም ሳይከፈል ሉዓላዊ ቦንድ ከጀመረ በእናት አገራችን ላይ እንደ ትልቅ ተራራ የሚቆለለዉን ብሄራዊ ዕዳ የምንከፍለዉ እኛ የዚህ ዘመን ኢትዮጵያዉያን ብቻ ሳንሆን ገና ያልተወለዱ የልጅ ልጆቻችን ጭምር ናቸዉ።

ኢትዮጵያ ኤኮኖሚዋ ያልዳበረ ደሃ አገር በመሆኗ አበዳሪ አገሮችን ብድር ሰርዙልኝ ብላ ሳትወተዉት፤ የብድር ክፊያ ግዜዋን ሳታራዝም፤ ወይም የብድር ዉል ማሻሻያ ጥያቄ ሳታቀርብ እስከዛሬ የተበደረችዉንና ለወደፊትም የምትበደረዉን የዉጭና የአገር ዉስጥ ብድር የመክፈል ሃላፊነቷን ጤናማ በሆነ መልኩ መወጣት የምትል አገር አይደለችም። እንደዚህ የምንለዉ ደግሞ ወያኔንና ዘረኛ ስርዐቱን ስለምንጠላ ሳይሆን በሚከተሉት ማስረጃዎች ላይ ተንተርስሰን ነዉ። 1ኛ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዕዳና አጠቃላይ አገራዊ ምርት (GDP) መጧኔ ቁጥሩ ከፍተኛ ነዉ።

ይህ ማለት ኢትዮጵያ የተቆለለባት ዕዳና ቤሄራዊ ገቢዋ ይቀራረባሉ፤ እኩል ናቸዉ ወይም ዕዳዋ ከገቢዋ ይበልጣል ማለት ነዉ። 2ኛ የአገራችን የዉጭ ብድርና የዉጭ ንግድ ገቢ መጣኔ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነዉ። ይህ ማለት ደግሞ ምርታችንን ለአለም ገበያ አቅርበን የምናገኘዉ የዉጭ ምንዛሪ ከዉጭ አገር ዕቃ ሊገዛልን ቀርቶ የተበደርነዉን ብድር ወለዱንም መክፈል አይችልም ማለት ነዉ። 3ኛ የወያኔ አገዛዝ የብድር ዕዳና አገዛዙ አገር ዉስጥ በግብር መልክ የሚሰበስበዉ ገቢ መጣኔ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነዉ። ቀለል ባለ አማርኛ የወያኔ አገዛዝ ሁሉንም ነገር ትቶ በሚሰበስበዉ ገንዘብ ዕዳዉን ብቻ ቢከፍል ከእዳዉ ለመላቀቅ ብዙ አመታት ይፈጅበታል።

ለእናት አገራቸዉ ለኢትዮጵያ የሚጨነቁ ኢትዮጵጵያዉያን የወያኔ ፓርላማ በቅርቡ ያፀደቀዉን የሉዐላዊ ቦንድ ሽያጭ ህግ አጥብቀዉ የሚቃወሙት እነዚህን ሁሉ ገሃድ የወጡ የአገራችንን ችግሮች በሚገባ ስለሚያዉቁ ነዉ። ለኢትዮጵያና ለህዝቧ እንጨነቃለን ስንል ደግሞ እንደ ወያኔ “እኔ ከሞትኩ ሥርዶ አይብቀል” በሚል የንፉጎች አባባል ተዉጠን አይደለም። ለትናንትናዋ ኢትዮጵያ እንደተጨነቅን ሁሉ ለዛሬዋ፤ ለነገዋና እኛ ካለፍን በኋላ ለሚመጣዉ ኢትዮጵያዊ ትዉልድም እኩል እንጨነቃለን። ለዚህም ነዉ የሉዓላዊ ቦንድ ሽያጩን ብቻ ሳይሆን ወያኔ ያመጣብንን መዐት ሁሉ ለማስቆምና አገራችንን በትክከለኛ የእድገትና የዲሞክራሲ መሠረቶች ላይ ለማስቀመጥ ወያኔ መወገድ አለበት ብለን የሞት የሽረት ትግል የጀመርነዉ።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org